# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 288 ህዳር 6 2006 ገጽ 1

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት ሰባት የቆመበት መሠረት ፅኑ፤ ዓላማውም ህዝባዊ ነው። በዚህ በፀና መሠረት ላይ ህዝባዊውን ዓላማ አንግበው የተነሱ ሚሊዮኖች አሉ። እነዚህ ሚሊየኖች የሌሉበት ሥፍራ የለም። ከቤተ-መንግስት እስከ እርሻ ማሳ፤ ከስለላ ተቋማት እስከ አገሪቷ መከላከያ ኃይል፤ ከሃይማኖት ተቋማት እስከ መንግስት መሥሪያ ቤቶች፤ ከዘመናዊ ትምህርት ተቋማት እስከ ተከበሩ ገዳማት ድርስ ለክብራቸው ዘብ የቆሙ ሚሊየኖች አሉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ላለው ጥቃት ተጠያቂው ወያኔ ብቻ ነው

መግለጫ

ወያኔ በትረ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ዓም ጀምሮ በአገራችንና በወገኖቻችን ላይ ከፈጸማቸው በርካታ ወንጀሎች አንዱ በህጋዊ መንገድ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ለባርነት ወደ አረብ አገራት በመላክ የአገራችንን መልካም ዝናና የህዝባችንን ክብር ያዋረደበት ተግባር ነው::

በወያኔ ንግድ ድርጅቶች ዋና ተዋናይነት ተመልምለው ለባርነት ሥራ የሚላኩትን ዜጎች በገፍ ስትቀበል የኖረቺው ሳውድ አረቢያ የሥራ ፍቃድ ያለቀባቸውን ከአገሯ ለማባረር ሰሞኑን በወሰደቺው የማዋከብ እርምጃ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን እየተደበደቡና ጎዳና ላይ እየተጎተቱ እሥር ቤት ታጉረዋል ፤ ገንዘባቸውን ተዘርፈዋል፤ ከፖሊስ የሚደርስባቸውን ድብደባና እንግልት ለመቋቋም የሞከሩት በግፍ ተገድለው አስከሬናቸው ጎዳና ላይ ተጥሎአል:: በርካታ ወጣት እህቶቻችን ደግሞ በአምስትና ስድስት የአረብ ጎረምሳ ወሲብ ጥቃት እየተፈጸመባቸው ለአካልና መንፈስ ጉዳት ተዳርገዋል:::

ይህ ሁሉ ሲሆን በአባይ ግድብ ግንባታ ሥም ገንዘብ ለመሰብሰብ ቦንድ ግዙ እያለ የሳውዲ ነዋሪ ሲጨቀጭቅ የኖረው በሳውዲ የወያኔ ኤምባሲም ሆነ አዲስ አበባ የሚገኙ ቅምጥል አለቆቹ ጥቃቱን ለማስቆም ድምጻቸውን ለማሰማት አለመፈለጋቸው ብቻ ሳይሆን ጥቃቱን ያደረሰውን የሳውዲ መንግሥት እርምጃ እውቅና የሚሰጥ መግለጫ በውጭ ጉዳይ ሚንስትር ቃል አቀባይ ዲና ሙፍቲህ መሰጠቱ እጅግ የሚያሳዝንና ሃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው::

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመላው አረብ አገር በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ያለው የባርነት ስቃይ በፋሺስት ጣሊያን ዘመን በወገኖቻችን ላይ ከተፈጸመው የከፋና በተለይ በሴት እህቶቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና መከራ እንደ አገርና እንደ ህዝብ የገባንበት ውድቀትና ውርደት ማሳያ ነው ብሎ ያምናል::

ስለዚህ ይህንን ውርደት ማስቆም የምንችለው ለዚህ ሁሉ መከራና ውርደት የዳረገንን የወያኔንሥርዓት ታግለን በማስወገድ በምትኩ ለአገሩና ለህዝቡ ፍቅር ያለው ፤ በያንዳንዱ ዜጋ ላይ የሚደርሰው መከራና ሲቃይ የሚቆረቁረው፤ አገር ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጥሮ ለባርነት ሥራ ወደ ውጪ የተላኩትን የሚሰበስብ መንግሥት ማቋቋም ስንችል ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ የግንቦት ሰባት መሪዎችን ለመግደል ያሰሬዉ ሴራ በመከሸፉ የኢትዮጵያ ህዝብ ደስተዉን እየገለጸ ነዉ

በወያኔው መረጃና ደህንነት ሃለፊ ጌታቸው አሰፋ እና በሃይለማሪያም ደሳለኝ አማካሪ ጸጋየ በርሄ ቁጥጥር የተመራና በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና በግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል መሪዎች ላይ የተቀነባበረው የግድያ ሙከራ መክሸፉን ተከትሎ ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ከሚገመተው በላይ ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል የሚያስችል የሰውም ሆነ የቴክኖሎጂ አቅም ያለው መሆኑን አስመስክሯል የሚሉ ተበራክተዋል። ይህን ሃሳብ የሚደግፉ ወገኖች ባንድ በኩል የፋሽስት ወያኔ አመራሮች ምንም እንኳ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ነው ያለነው ቢሉም ምን ያህል የተዋረደና የቀለለ ስራ ለመስራት እንደሚደፍሩ በግልጽ በራሳቸው አንደበት የሰማንበትና ያወቅንበት ነው ሲሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ራሱን ለመከላከል የሚያስችለውን ቴክኖሎጂያዊ አቅም መገንባቱንና ይህም ለሀገራችንና ነጻነት ለጠማው ሕዝባችን ታላቅ ተስፋ ሰጭ ነው ሲሉ ተደምጠዋል።

ሌሎች በጉዳዩ የተደሰቱ ወገኖች ደግሞ ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊትም ለገንዘብና ለስልጣን የሚጓጉ ለሕዝብ ልእልና ደንታ የሌላቸው እና ለማይገኝ ባዶ ምኞት የሞቱ ሆዳሞችን በመግዛት ስንት የሕዝብ ተሰፋ እንቅስቃሴዎችን እንዳደናቀፉ አስታውሰው ይህ ግን ልዩ ነበር ካሉ በኋላ ወያኔዎች የት ደረጃ ላይ እንዳሉና አቅማቸውም እስከምን ድረስ እንደሆነ አወቅንበት ይላሉ። ከዚህ በፊት በተለይ በ1997 ዓ/ም የነበረውን ምርጫ ቅንጅት ቢያሸንፍም ፋሽስት ወያኔ ገልብጦ ሁሉን ለራሱ በማድረግ እንዲጫወት እገዛ ያደረጉለት የሕዝብ ወገን ነን እያሉ በመደለል በሆዳቸውና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች የተገዙ ከሃዲዎች እንደነበሩ አይዘነጋም።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ትግሉ መሯል፤ እኛም ዝግጁዎች ነን

መግለጫ

በንቅናቄዓችን ፀሐፊ እና በግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል አመራር አባላት ላይ የተቃጣው ረዥም ጊዜ የወሰደ የግድያ ሴራ መክሸፉ አስደስቶናል። ይህ ሴራ የወያኔ የስለላና የግድያ ኃላፊዎች በሆኑት ጌታቸው አሰፋ እና ጸጋየ በርሄ የቅርብ ክትትል የተመራ፤ የአሻንጉሊቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሣለኝ እውቅናና ይሁንታ የተሰጠው፤ ወያኔ ከፍ ያለ ተስፋ የጣለበት ሴራ ነበር።

"ወያኔ-ኦ-ሚሊኒየም" የተሰኘው ይህ በወያኔ የመጨረሻ ከፍተኛው አመራር የተመራው ሴራ ስለወያኔ ውስጣዊ አደረጃጀት ጠቃሚ መረጃዎችን ሰጥቶናል። ከዚህም በተጨማሪ የወያኔ ሹማምንት ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ንቀት፤ ከአመት በኋላ ስለሚደረገው ምርጫ ውጤት፤ ለሰላዮቻቸው ስለሚሰጡት ጉርሻ መጠን፤ እና ሌሎችም በርካታ ጉዳዮች ተስፋ ከጣሉበት ቅጥረኛ ነብሰ ገዳያቸው ጋር ካደረጉት የስልክ ንግግሮች ማድመጥ ይቻላል። ይህ ለበርካታ ጥናቶች በግብዓትነት ሊውል የሚችለውን በድምሩ ከስምንት ሰዓታት በላይ የሚፈጀው የስልክ ንግግር ቅጂ በሕዝባዊ ኃይሉ የመረጃ ክፍል አማካይነት ለሕዝብ በኢንተርኔት በነፃ ተለቋል። በአጋጣሚውም የወያኔ ገበና ተጋልጧል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የወያኔ የሽብር ጥቃት ማስጠንቀቂያ በሕዝቡ ላይ የተነዛ ሌላ ሽብር እንደሆነ ተጠቆመ

ወያኔ ሀገራችንን ያሸባሪዎች ጥቃት ያሰጋታል ማለቱን ተከትሎ በሕብረተሰቡ ውስጥ አለመረጋጋትና ሽብር መንገሱን የሚገልጹ ጥቂቶች አይደሉም። በእርግጥ አደጋው ካለ ለሕዝብ ከመገለጹ በፊት ርምጃው መወሰድ ነበረበት የሚሉ ወገኖች ምንም ባልታየበት ሁኔታ በሁሉም የወያኔ መዲያዎች ሽብር አለ ተጠንቀቅ ማለት ሕዝብ ከማሸበሩም በላይ ሀገር እየመራሁ ነው ከሚል አካል አይጠበቅም ይላሉ።

"ፋሽስት ወያኔ የደህንነት ሰዎች የሚላቸው ስራቸው ምንድን ነው? እቅድ ካለ እንኳ የታቀደ ጥቃት ሁሉኮ ተፈጻሚ አይሆንም" የሚሉ ሌሎች ወገኖች ደግሞ በእርግጥ የሽብር ጥቃት ካለ በሚስጥር ተይዞ አስተማማኝ በሆነ ጊዜ ከአደጋ አድራሶቹ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል ከሚባሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር አደጋውን ማክሸፍ ይቻል ነበር እንጅ በዚህ መልኩ ራሰቸው ፈርተው ሕዝብን ጭምር ማስፈራራትና ማሸበር ሕዝብን አስተዳድራለሁ እያለ ሌት ከቀን ከሚገዘት አካል የሚጠበቅ አይደለም ይላሉ። ምንም እንኳ ፋሽስት ወያኔ የሽብር ስጋት አለብኝ ቢልም ንብረት እያወደመና በግልጽ ሕዝብ እያሸበረ የሚገኘው ራሱ ወያኔ መሆኑ ግን ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች መዘገቡ ይታወሳል።

## ኢትዮጵያውያን በሳውዲ አረብያ በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ባለው ጥቃት ቁጣቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው

በሳውዲ አረብያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የመንግስት ፖሊሶችና ህዝቡ ባደረሰባቸው ጥቃት በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቁጣቸውን ማሰማታቸውን ቀጥለዋል። በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞችና በአሜሪካ ዋሺንግተን ዲሲ ባለፈዉ ሐሙስ በሳውዲ አረብያ ኤምባሲ በመገኘት ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ እንደተደረገ ለማወቅ ተችሏል።ይህ በንዲህ እንዳለ የግንቦት 7 የፍትህና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በዜጎቻችን ላይ የደረሰውን ጥቃት በተመለከተ መግለጫ ያወጣ ሲሆን በመግለጫው በሳውዲአረብያ በወገኖቻችን ላይ እየተፈጸመ ላለው ጥቃት ተጠያቂው የወያኔ ጉጅሌ ብቻ እንደሆነ ገልጾ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ለባርነት ወደ አረብ ሐገራት በመላክ የሀገራችንን መልካም ዝናና የህዝባችንን ክብር አዋርዷል ብሏል ግንቦት 7 በመግለጫው። ግንቦት 7 የፍትሕና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ይህን መሰሉ ሐገራዊ ውርደት እንዲያበቃ የወያኔን ጉጅሌ ለማስወገድ የጀመርነውን ትግል ተቀላቀሉን በማለት በድጋሚ ጥሪ አቅርቧል።

ሳዉዲ ዉስጥ የሚገኘዉ የወያኔ ኤምባሲ ዛሬ በሳዉዲ መንግስትና ህዝብ ከፍተኛ ጥቃት የሚደርስባቸዉን ኢትዮጵያዉያን ለአባይ ግድብ ግንባታ ገንዘብ አምጡ እያለ ይጨቀጭቃቸዉ እንዳልነበረ ዛሬ ግን ኢትዮጵያዊነታቸዉን ብቻ ሳይሆን ሰዉ መሆናቸዉን ጭምር ረስቶ ከበዳዮቹ ከሳዉዲ ባለስልጣኖች ጋር እጅና ጓንት በመሆን ወገኖቹ ሲበደሉ ታዛቢ ሆኖ መመልከት ጀምሯል። የሳዉዲዉ የወያኔ ኤምባሲም ሆነ አዲስ አበባ የሚገኙ ዘረኛ አለቆቹ ሳዉዲ ዉስጥ በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰዉን ጥቃቱ ለማስቆም ድምጻቸውን ከማሰማት ይልቅ ጥቃቱን ያደረሰውን የሳውዲ መንግሥት እርምጃ እውቅና የሚሰጥ መግለጫ በውጭ ጉዳይ ሚንስትር ቃል አቀባይ ዲና ሙፍቲህ በኩል በመስጠት የኢትዮጵያዉን ጠላት መሆኑን አስመስልሯል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አንድ አንዳርጋቸውን መግደል የነፃነቱን ትግል ማስቆም አይቻልም

የጠቅለይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ አዲሱን የወያኔ ዘመቻ በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማማከር ወደ ቢሯቸዉ ሄዶ ግንቦት ሰባትን በተመለከተ እቅዳችንን ልነግሮት ነዉ የመጣሁት ሲል ንግግሩን ጀመረ።

እሺ ምንድ ነው እቅዱ ?

የአንዳርጋቸውን፤ ጓደኞቹንና አንዳንድ የኤርትራ ባለስልጣኖችን ለመግደል ዝግጅቱ ተጠናቋል። ኤርትራ ድረስ ሂዶ "መስዋዕትነት" ለመክፈል የሚችል አንድ ሰው አግኝተን ልከናል። ግዳጁን ፈፅሞ ሲመጣ አንዳንድ ነገሮች እናደርግለታል። እርሱም ተስማምቷል። ጥቅምት 28 የምስራች እንሰማለን። እስከዛው ግን ፍተሻዎች እንዲጠናከሩ ወጥተህ ተናገር።

ሰውየው "already" ተልኳል ማለት ነው ?

አዎን ከተላከ አምስት ወር ሁኖታል።

የሚሳካ ይምስላችኋል ?

አዎን . . በሚገባ! እኛ ሞክረነዉ ያልተሳካ ምን ነገር አለ? . . . ጌታዬ። በደንብ ነው የሚሳካው። ዛሬ እዚህ መጥቼ የማሳስብዎት ይህ ጉዳይ ሲታቀድም ሲፈጸምም አልሰማሁም ብለዉ እንደ እግር ኳሱ እንዳያሳፍሩን ብዬ ነዉ።

አይዟችሁ እናንተም አታሳፍሩኝም እኔም አላሳፍራችሁም። እሺ ሰምቼያለሁ። አለ "አማኝ ነኝ ባዩ" ደሳለኝ ኃ/ማሪያም ምንም ዓይነት ወንጀል ያልሰሩ የአገሪቷ ምርጥ ልጆች ደማቸው በከንቱ እንዲፈስ እየተስማማ።

"ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ንጣት በገደለው "ሲሉ አመሳጠሩ የሃገራችን ሰዎች።

"ቀፎው ነው እንጂ ሲም ካርዱ ከእኛ ነው" የተባለለትና እና በነፍስ ገዳዮቹ ወንበር የተቀመጠውን የደሳለኝ ኃ/ማሪያምን ጉዳይ በዚህ እናበቃለን።

ህወሃቶች የንጹሃን ዜጎችን ደም በከንቱ ሲያፈሱ የኖሩ ነብሰ ገዳዮች እንደሆኑ የሚታወቅ ነው። አሁንም ክብሬንና ነፃነቴን የሚሉ ዜጎችን ይዘው ደብዛቸውን ለማጥፋት ብዙ ዓይንና ብዙ ጆሮዎችን በየቦታው አቁመናል እያሉ ያቅራራሉ። ይሄን ሁሉ ዓይንና ጆሮ ይዘንስ የሚያሸንፈን ማን ነው ? ሲሉም ይደመጣሉ። እነርሱ እንደሚሉት ዓይኖቻቸው ማየት፤ጆሮዎቻቸውም መስማት የሚችሉ አይደሉም። የህወሃት ዓይኖች ማየት የተሳናቸው እውራን፤ ጆሮዎቻቸውም ማድመጥ የማያውቁ ደናቁርት እንደሆኑ የታወቀ ነው። ህወሃቶች ይህን የማይሰማ ጆሮና ፤ማየት የተሳነውን ዓይን ይዘው እየተደናበሩ፤ ይህን ለመደበቅ ህይዎት ያላቸው መስለው ይታያሉ። አዎን ህወሃቶች ጭው ባለ በርሃ ላይ ብቻችሁን እንደቆማችሁ እወቁ። የሚነገረው እና የሚሆነው በሙሉ ስለተሰወረባችሁ በብዙ ሚሊየኖች መሃከል ብቻችሁን እርቃናችሁን ቀርታችኋል። ብዙ ሚሊዮን ዓይኖች እና ጆሮዎች በእናንተ ላይ መተከላቸውን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነፃነት እና የእኩልነት ንቅናቄ እንደ ህወሃት-ኢህአዴግ ጆሮዉ የተደፈነና አይኑ የታወረ ድርጅት አይደለም። ግንቦት ሰባት ንቅናቄ የሚያይ ዓይን፤ የሚሰማ ጆሮና የሚያስተዉል ልቦና ያለው ህያው ንቅናቄ ነው። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጥያቄ ግልፅ ነው። ነፃነት ! ፍትህ ! እና ዲሞክራሲ ! ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች በአግባቡ መልስ እንዲያገኙ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል ተነስተናል ጉዞ ጀምረናል፤ ሺ አንድአርጋቸውን ፈጥረናል። ልብ ይበሉ ነፃነት ፍትህ እና ዴሞክራሲ ለሰው ልጆች የተሰጡ ክቡር ስጦታዎች ናቸው። ህወሃት እነዚህን ክቡር ስጦታዎች ከዜጎች ላይ ነጥቆና ህዝብን ረግጦ መቀጠል የለበትም። ህወሃት የዜጎችን ነፃነት ነጥቆ ፤ ፍትህን አጓድሎና ህዝብን ረግጦ እንደከዚህ በፊቱ በሠላም እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ ከሆነ ተሳስቷል። በህወሃት ቅዥት አገራችን ተጎድታለች። ህዝቧም ለማያባራ ጉስቁልናና ውርደት ተዳርጓል። ብዙዎችም አገር አልባ ሁነው በየሰው አገሩ መፃተኛ ሁነው እንዲኖሩ ተገደዋል። በእኛ እምነት በአገራችን ላይ እየደረሰ ላለው ውርደት በዋናነት ተጠያቂው ህወሃት ነው። ህወሃት የኢትዮጵያ ዋነኛው ጠላት ነው የምንለውም ዜጎቻችንን ለጉስቁልናና ለውርደት ስላደረገም ጭምር ነው። እኛ ይህን አገር በቀል ጠላት ከሥሩ ነቅለን ለመጣል ተነስተናል። ከዚህ ትግል የሚያቆመን ምንም ዓይነት ምዳራዊ ኃይል እንደሌለ ህወሃቶች እንዲያውቁት እንፈልጋለን። ህወሃቶች አንገታችንን አስደፍተው አይገዙንም። ጥቁር ደም ያፈራቻቸው የቁርጥ ቀን ውድ ልጆቿ የነጻነት ታሪክ በጥቁር ቀለም ይጻፍ ዘንድ የሚያደርጉትን ሀገርን የማዳን ጥሪ እንዲህ በቀላሉ መግታት ከቶ አይቻልም። ወያኔዎች አትደናበሩ! ጋሬጣውን መለየትን ለእኛ ተውሉን።

ታዲያ ይህን ንቅናቄ አንድ አንዳርጋቸውን በመግደል ማስቆም የሚቻል የሚመስለው ጅላ ጅል ቡድን አገሪቷን እየገዛ በመሆኑ ተቆጭተናል። አንዳርጋቸውን መግደል ሌሎች በርካታ ኢትዮጵያዊ አንዳርጋቸውን መፍጠርና ትግሉንም የሚያጠናክር እና የሚያፋፍም መሆኑን አልተረዱም። የኢትዮጵያ ህዝብ የእምቢተኝነት፣ የአልገዛም፣ የነጻነት ታሪክን ለማስከበር መሰዋእትነትን ለመክፈል ዝግጁ መሆንን ከአንዳርጋቸው ከተማረ ቆይቷል። መቆጨታችን ግን እንዲሁ በቁጭት ብቻ የሚቀር የሚመስለው ካለም ድግሞ ተሳስቷል። ይሄ ቁጭት በየደረሱበት የንፁሃንን ደም በከንቱ ማፍሰስ አገር መምራት የሚመስላቸውን ህውሃቶች ከተንጠለጠሉበት ዙፋን አውርደን በልካቸውና በአቅማቸው እንዲኖሩ ለማድረግ የጀመርነውን ትግል ይበልጥ አጠናክረን እንድንቀጥል ያደርገናል። ህወሃት ውስጥ እንደ ሰው ማሰብ የሚችል ግለሰብ ካለ አሁን ቆም ብሎ እንዲያስብ እናሳስበዋለን። ጀንበር ሳትጠፋባችሁ ለነጻነት፣ ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገውን ትግል ተቀላቀሉ። እርግጥ ነው ለነፃነት የሚደረገው ትግል በየመስኩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና ህወሃትም የእጁን እንደሚያገኝ ምንም ዓይነት ብዥታ እንዳይኖራችሁ ልንነግራችሁ እንወዳለን።

ግንቦት ሰባት የቆመበት መሠረት ፅኑ፤ ዓላማውም ህዝባዊ ነው። በዚህ በፀና መሠረት ላይ ህዝባዊውን ዓላማ አንግበው የተነሱ ሚሊዮኖች አሉ። እነዚህ ሚሊየኖች የሌሉበት ሥፍራ የለም። ከቤተ-መንግስት እስከ እርሻ ማሳ፤ ከስለላ ተቋማት እስከ አገሪቷ መከላከያ ኃይል፤ ከሃይማኖት ተቋማት እስከ መንግስት መሥሪያ ቤቶች፤ ከዘመናዊ ትምህርት ተቋማት እስከ ተከበሩ ገዳማት ድርስ ለክብራቸው ዘብ የቆሙ ሚሊየኖች አሉ። እነዚህ ሚሊኖች የቆሙት መረቅ የበዛበትን ወጥ ዓላማ አድርገው ሳይሆን በፀናው መሠረት ላይ ለተተከለው ክቡር ዓላማ ነው። ይህ ክቡር ዓላማ ነፃነት፤ ፍትህ ፤እኩልነት እና የህግ የበላይነት እንጂ ሌላ አይደለም። እነዚህ ሚሊየኖች አትኩረው ማየት የሚችሉ ድንቅ ዓይኖች ያሏቸው፤ አጥርተው ማድመጥ የሚችሉ ክቡራን ጆሮዎች ያሏቸው መሆናቸውን ህወሃቶች እንዲያውቁት እንወዳለን።

ግንቦት ሰባት ማንንም ፍርሃት እና ድንጋጤ ውስጥ መክተት አይፈልግም። እንዲያውም ግንቦት ሰባት ንቅናቄ የሚታገለው ዜጎች ሁሉ ከፍርሃት ነፃ ሁነው በደስታ እንዲኖሩ ለማስቻል ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ካሁን ወዲያ ከግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዓይንና ጆሮ የሚያመልጥ አንዳችም ነገር እንደማይኖር የሚያሳድደን ቡድን እንዲያውቀው እንፈልጋለን። ዓይንና ጆሯችን በሁሉም ሥፍራ በንቃትና በጥንቃቄ ነገሮችን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

ህወሃቶች ከትዕቢታችሁ ብዛት የተነሳ የህዝቡን ምክር መናቃችሁን እናውቃለን።የወገኖቻችንንም ድምፅ ጫጫታ እያላችሁ እንደምትሳለቁም እናውቃለን። ይሄ እንደማይጠቅማችሁ ብዙ ግዜ ነግረናችኋል። የህዝቡን ምክር ስሙ፤ የወገኖቻችሁንም ድምፅ አድምጡ ብንላችሁ በእምቢታችሁ ፀንታችኋል። ልቦናችሁ እንደ ፈርዖን ልብ ደንድኗል።ልብ ማደንደን እንኳን እናንተን ለመሠለ ደካማ ፍጡር ይቅርና በዘመኑ እኔ "እምላክ" ነኝ እሰከ ማለት ለደረሰው ለፈርዖንም አልበጀም። እንዲህ ዓይነት የልብ ድንዛዜ እናንተ በዚያ ጠባብ ዓላማችሁ ጣልነው ለምትሉት ለመንግስቱ ኃ/ማሪያምም አልረባውም። አሁንም የእኛ ምክር አጭርና ግልፅ ነው። የመዘዛችሁትን የበቀል ሰይፍ ወደ ሰገባው መልሱ። የዘጋችሁትን በር ክፈቱ። የነጠቃችሁትን የዜጎች ነፃነት መልሱ። በህዝቡ ላይ ያወረዳችሁትን የፍርሃት ድባብ አስወግዱ። የተከላችሁትን የዘረኝነት እሾህ ንቀሉ። ከእውነት ጋርም ታረቁ። እንዲህ ብታደርጉ የዚያችን አገር በረከት ትበላላችሁ፤ እምቢ ብትሉ ግን የሚበላችሁን እሳት ማጥፋት አይቻላችሁም። መጥተናል!!

እኛም ከምን ግዜውም በላይ ተጠናክረናል። የትግል ዘርፋችን ሰፍቷል። በሁሉም አቅጣጫ መረባችን ተዘርግቷል። ከዚህ መረብ የትም አታመልጡም። ማምለጫ መንገዳችሁ አንድ ብቻ ነው። እርሱም የህዝቡን ድምፅ መስማት፤ እውነተኛ መልስ መስጠት እና ለህግ ተገዢ መሆን። አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መሆኑ ታውቆ ወያኔን ለማስወገድ የተጀመረውን ትግል በተለይ ወጣቱ የህብረተሰባችን ክፍል በነቂስ እንዲቀላቀል፡ የተቀረውም ህዝባችን አቅም የፈቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ ግንቦት 7 የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

በመጨረሻም ምንም እንኳ በተለያዩ አረብ አገሮች በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ላለው መከራና ስቃይ ዋና ተጠያቂው ዜጎችን በህጋዊ መንገድ ለባርነት ከላከ ቦኋላ ጥቃት ሲፈጸምባቸው መከላከል ሳይፈልግ ዝም ብሎ እየተመለከተ ያለው የወያኔ አገዛዝ መሆኑ ባያጠያይቅም፡ የሳውዲም ሆነ ሌሎች አገሮች ተቆርቋሪ በለላቸው ዜጎቻችን ላይ የሚፈጽሙትን ወንጀል በአሰቸኳይ እንዲያቆሙና ተጠያቂዎቹንም ለህግ እንዲያቀርቡ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄን አቅም የፈቀደውን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሁሉ ወያኔን ከማስወገድ ትግል ጋር አጣምሮ እንደሚገፋ ይገልጻል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

---

## በሬ ሆይ ሳር ሳሩን አየህ ገደሉን ሳታይ

በወያኔዉ የደህንነት ሹም በጌታቸዉ አሰፋ ተጠንስሶ በይስሙላዉ ጠቅላይ ሚኒስቴር በኃ/ማሪያም ደሰላኝ ቡራኬ ተጀምሮ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዋና ፀሀፊ የሆኑትን አቶ አንድአርጋቸዉ ጽጌን ለመግደል ላለፉት አምስት ወራት በእንቅስቃሴ ላይ የነበረዉ ዘመቻ ወያኔ ኦ ሚሊኒየም ከሸፈ። ከግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይሎች በተገኘዉ መረጃ መሰረት ይህንን የወያኔ የተቀነባበረ የግድያ ዘመቻ ሲጠነሰስ ጀምሮ እስካለፈዉ ሐሙስ ህዳር 28 ቀን ድረስ ተከታትሎ ያከሸፈዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይሎች የመረጃና የደህንነት ክንፍ አንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። አድማጮቻችን ይህ ዜና ባለፈዉ ሳምንት በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያንን ብዙ ያስፈነጠዘ፤ ያነጋገረና ብዙም ያሳሰበ በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔን ባዶነትና የእምቧይ ካብነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየና የወያኔ ነብሰ ገዳዮች ከህዝብ ኃይሎች ጋር ፊት ለፊት ሲገጥሙ ፀሐይ እንደገላመጠዉ በረዶ ቀልጠዉ የሚጠፉ ምናምንቴዎች መሆናቸዉን ያበሰረ ሰበር ዜና ነበር። ይህ ዜና ከተመሰረተ ገና አንድ አመት ያልሞላዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል "ተራሮችን አንቀጠቀጥኩ" ብሎ ሲፎክር የሰነበተዉን የወያኔ ኃይል በፍርሀት አንዲንቀጠቀጥ በማድረጉ የኢትዮጵያ ህዝብ እደግ ተመንደግ ብሎታል፤ በጉብዝናዉ ተመክቶበታል በተለይም ታንክና አዉሮፕላን ታጥቅያለሁና አትሞክሩኝ እያለ ከሃያ አመት በላይ ህዝብን ሲያስፈራራ የነበረዉን ወያኔን በማስተንፈሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ኮርቶበታል።

"ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል" ይላል የአገራችን ሰዉ። ይህ ተረት የተተረተዉ ወያኔ ከመፈጠሩ በፊት ቢሆንም ተረቱ ትክክለኛ ቦታዉን ያገኘዉ ግን ወያኔ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ ነዉ። ወያኔና ጅራፍ አንድ ናቸዉ፤ሁለቱም እራሳቸዉ ገርፈዉ እራሳቸዉ ይጮሃሉ። የወያኔን አንደ ጅራፍ ገርፎ መጮህ ለማረጋገጥ ምስክር መሰብሰብ የሚያስፈልግ አይመስለንም፤ ባለፉት አራትና አምስት አመታት አዲስ አበባ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች እራሱ የቀበረዉን ቦምብና ፈንጂ እሱ እራሱ አፈንድቶት በተቃዋሚዎች እንደሚያሳብብ ምዕራባዉያን የነብስ አባቶቹን በእማኝነት መጥቀሱ ይበቃል። ወያኔ በቅርቡ አዲስ አበባ መርካቶ ዉስጥ የቴሌቭዥን ካሜራ ደርድሮ በሰራዉ ድራማ እሱ እራሱ ጉድጓድ ቆፍሮ የቀበረዉን ፈንጂ ተራ በተራ እየቆጠረ ሲያወጣ ተመልክተናል። ወያኔ እንደዚህ አይነት ተነግሮ የማያልቅ ብዙ ድራማዎች አሉት። እራሱን መንግስት ብሎ የሚጠራዉ ወያኔ ባለፈዉ ሳምንት ሊያሳየን የነበረዉ ድራማ ግን እንኳን አገር ከሚመራ አካል ከተራ የመንደር ዉስጥ አዉደልዳዮችም የሚጠበቅ አይደለም። በእርግጥም ወያኔና ቅጥረኛዉ ሙሉቀን መስፍን አምስት ወር ሙሉ ተለማምደዉ ባለፈዉ ሐሙስ ህዳር 28 ቀን 2006 ዓም ሊከዉኑት የነበረዉ ነገር ግን መጋረጃዉ ሳይከፈት በነበር የቀረዉ ትዕይንት ሞኝና ዕብድ ያቀነባበሩት ድራማ ነዉ። አዎ! ዘመቻ " ወያኔ ኦ ሚሊኒየም" እንደ አኬል ዳማና ጂሃዳዊ ሀረካት ለኢቲቪ መስኮት ሳይበቃ የበረሃ ሽታ ሆኖ የቀረ ከያኒ የሌለበት ድራማ ነዉ።

እሱ እራሱ የቀበረዉን ቦምብና ፈንጂ እያፈነዳ ህዝብን "ሽብርተኞች መጡብህ" እያለ ማስፈራራት የለመደዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ ረቡዕ ህዳር 27 ቀን ለመላዉ ኢትዮጵያ ህዝብ በሬድዮና በሌቪዥን ባስተላለፈዉ መልዕክት አልሸባብና በኤርትራ የሚደገፉ ሀይሎች በመላው አገሪቱ ጥቃት ለመፈጸም እየተዘጋጁ ለመሆናቸዉ አስተማማኝ መረጃ አለኝ በማለት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነቅቶ አካባቢዉን አንዲጠብቅና እራሱን ለመከላከል አስፈላጊውን ዝግጁ እንዲሆን ማሳሰቡ የሚታወስ ነዉ። ሆኖም እነዚህ ተራ ዱሪዬዎችና የመንደር ዉስጥ አዉደልዳዮች የኢትዮጵያን ህዝብ ሽብር ተደግሶልሃል እያሉ ያስፈራሩት እነሱ እራሳቸዉ ኤርትራ በረሃ ዉስጥ የደገሱት ሽብር የሚሳካ መስሏቸዉ "ይኼዉልሃ" ደረስንልህ ሊሉት ነበር። ሆኖም ነገሩ "እዛም ቤት እሳት አለ" ነዉና ጀግኖቹ የግንቦት ሰባት የመረጃና ደህንነት ክፍል ሰራተኞች የወያኔን የሽብር ሙሽራና ሙሽሪት የሰርጋቸዉ ቀን ከመድረሱ በፊት በቁጥጥር ስር ማድረግ በመቻላቸዉ በዘመቻ "ወያኔ ኦ ሚሊኒየም" ስም የወያኔን ጀግንነትና አይደፈርነት እንዲያሰይ የታቀደዉ ድራማ በተቃራኒዉ የወያኔን ትንሽነትና ተራ ሽፍታነት በማሳየት እንዳልነበረ ሊሆን ችሏል። የወያኔዎች ሀሳብና ምኞች አንዳርጋቸዉ ጽጌን ገድለዉ "ልማታዊ የግድያ ሴራቸዉን" በልማታዊ የክኒት ሰዎቻቸዉ አጅበዉ አንደ መንግሰቱ ኃ/ማሪያም የፍየል ወጠጤ ሊዘፍኑብን ነበር፤ ነገር ግን "ስለት እራሱን ደባ ድጉሱን" ነዉና እራሳቸዉ በደገሱት ድግስ "ጉሮ ወሸባዬ" ተዘፍኖባቸዋል።

ወያኔዎች በእነሱ ቤት ጥቅምት 28 ቀን የኢትዮጵያን ህዝብ ከሽብርተኞች እራስህን ጠብቅ ብለዉ አስጠንቅቀዉ ጥቅምት ሰላሳ ቀን ደግሞ የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋና ፀሀፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌን ገድለዉ ህዳር ሲገባ "ተራሮችን ያንቀጠቀጠዉ ትዉልድ" ታሪክ ደገመ ሊሉን ነበር። ደግነቱ ብርቱ ነኝ ብሎ ለሚፎክር ሁሉ ለእሱም ብርቱ አለዉና ለህዳር መግቢያ የደገሱት ድግስ ህዳር ሳይታጠን ደጋሾቹ እራሳቸዉ በግንቦት ሰባት ኃይሎች ታጥነዉ እንደጉም በንነዉ ጠፍተዋል። ከወገኖቹ ጎን ተሰልፎ ጠላቶቹን መታገል የነበረበት ሙሉቀን መስፍን የተባለ ከሀዲ ግለሰብም እነዚያ ከሃዲ አዛዦቹ ቃል በገቡለት ስፍር ቁጥር በሌለዉ ኃብት ምትክ ሰንሰለትና እግረ ሙቅ ተሸልሞ የእስር ቤቱን ኑሮ ጀምሮታል። በጠቅላይ ሚኒስቴር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ፤ በደህንነት ሹሙ ጌታቸዉ አሰፋና በጠ/ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ በጸጋዬ በርሄ ተጠንስሶ የሽብር ስራዉን የጀመረዉ ዘመቻ "ወያኔ ኦ ሚሊኒየም" "ሚሊኒየም ዋ ወያኔ" በሚል የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ማስጠንቀቂያ ተደምድሟል።

በ1967 ዓም እግሩ ደደቢት በረሃን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ በገደላቸዉ ሰዉ ደም ላይ ተራምዶ ዛሬ ላይ የደረሰዉ ወያኔ ዛሬም አገር እየመራ ሰዉ መግደሉን አላቆመም። ወያኔ ሰዉ መግደል አቆመ ማለት የስልጣን ዘመኑ አበቃ ማለት እንደሆን በሚገባ ያዉቃል፤ ስልጣን አንዴ ከእጁ ወጥቶ ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ እጅ ከገባ ደግሞ ወያኔ እንዳሻዉ ቢንጠራራ እንደገና እንደማያገኘዉም በሚገባ ያዉቃል፤ ስለዚህም ነዉ የኢትዮጵያን ህዝብ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ የሚታገሉ ኃይሎችን አገር ዉስጥም ይሁን ከአገር ዉጭ ባሉበት ቦታ ሁሉ እየሄደ ሊያጠፋቸዉ የሚሞክረዉ። ሆኖም ይህ ከሩሲያና ከዩክሬይን የሚገዛቸዉ ዘመናዊ ልዕለ ድምጽ የጦር አዉሮፕላኖች ሰማይ ቤት የሚያደርሱት መስሎት "ሰማይ ቤት ብትሄዱም አታመልጡኝም" ብሎ የደነፋዉ ዕብሪተኛዉ የወያኔ አገዛዝ እዚሁ ምድር ላይ አፍንጫዉ ስር ያለ ኃይል እንደ አሻንጉሊት ሲጫወትበት ተይቷል። ወያኔ ያሻዉን ያክል ሰዉ መግደልና ማሰር ይችል ይሆናል፤ ህዝባዊ አላማችንንና ህዝባዊ ትግላችንን ግን ማሰርም መግደልም አይችሉም። ግንቦት ሰባት እንደ ወያኔ "በአንድ ለእናቱ" መሪ የሚመራ ድርጅት አይደለም። ግንቦት ሰባት የትግሉን መራራነትና የሚያስከፍለዉን የመስዋዕትነት ደረጃ ተረድቶ የተመሰረተ ንቅናቄ ነዉ። ግንቦት ሰባት መቶ መሪዎች ቢገደሉበት ሁለት መቶ መሪዎችን በቀኖች ዉስጥ መተካት የሚችል ድርጅት ነዉ። ወያኔም ቢሆን ከዚህ ሳይጀመር ከከሸፈዉ ፀረ ህዝብ ዘመቻ መማር የሚገባዉም ይህንኑ ነዉ። ወያኔ የነፃነት ታጋዮችን በገደለ ቁጥር የትግሉን ጎራና አድማስ ከማስፋትና የራሱንም የስልጣን ዘመን ከማሳጠር የዘለለ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ አይችም። ወያኔዎች እብሪተኞች፤ ትዕቢተኞችና ዉሸታሞች እንደሆኑ እናዉቃለን፤ ሆኖም ምንም ቢሆን የወያኔ መሪዎችም ሰዎች ናቸዉና "በቅሎ ገመዷን በጠሰች ቢሉ በራሷ አሳጠረች" የሚለዉን የዚያችን መካን እንስሳ ስህተት የሚደግሙ አይመስለንም።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ጥርስ የሌለዉ አንበሳ መሆኑን እሱን እራሱን ጨምሮ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚያዉቀዉ ሀቅ ቢሆንም ኃ/ማሪያም በትምህርት ደረጃዉ፤ በግብረገብነቱና በክርስትና እምነቱ ከእሱ በፊት በተከታታይ ኢትዮጵያን ከመሩ ሁለት አምባገነኖች ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም የተሻለ ሰዉ ነዉ። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ጠንካራ ጎን ነዉ ተብሎ የሚታመነዉ ከልቡ አምኖበት የፈጠረዉን አምላክ የሚያመልክ ሰዉ መሆኑ ነዉ። እንግዲህ ይህ እግዚአብሄርን ይፈራል የተባለለት ሰዉ ነዉ አትግደል የሚለዉን የእግዚአብሄርንና የፈጣሪዉን ትዕዛዝ ረግጦና የምድር ላይ ጌቶቹን ትዕዛዝ ተቀብሎ ሄዳችሁ ግደሉ ብሎ ብሎ ለነብሰ ገዳዮች ቡራኬ የሰጠዉ። ከሰሞኑ አንድ የወያኔ የደህንነት ሰራተኛና አንዳርጋቸዉን እንዲገድል የመለመሉት ከሀዲ ሰዉ በስልክ ያደረጉትን ምልልስ እንዳዳመጥነዉ የወያኔ ነብሰ ገዳዮች ጠ/ሚ ኃ/ማሪያም ቢሮ ድረስ ሄደዉ "የአንዳርጋቸዉን ራስ በሳህን አድርገን እናመጣልሀለን" ብለዉ ሲነግሩት . . . አሜን ይቅናችሁ ብሎ ለነብሰ ገዳዮች መልካም ምኞች እንደተመኘ ሰምተናል። ከአህያ ጋር መዋል የግድ አህያ ባያደርግም አህያ ሊያስመስል ይችላል፤ ግን የሰዉ ልጅ እንኳን ከአህያ ጋር ከምንም ጋር ቢዉል እንዴት ማንነቱን ይረሳል? እንዴትስ አገርን ያክል ትልቅ ነገር የሚመራ ሰዉ በሚመራዉ ህዝብ ፊት ገሀድ አይደለም ህልም ነዉ ብሎ ያጣጣለዉን ባለጋራ በገሀዱ አለም በህልሙ ሳይሆን በዉኑ ካልገደልኩህ ብሎ ያሳድደዋል?

የግንቦት ሰባት ኃይሎች በሚስጢር በቀዱት የስልክ ምልልስ ዉስጥ ሙሉቀን መስፍን ወይም ቄሴ፤ አንገረብና ከአዲስ አበባ አምሀጅር ድረስ የዘለቀዉ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣን ያደረጉትን የሦስትዮሽ የስልክ ንግግር ያዳመጠ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወያኔዎች ምን ያህል ዘረኞች፤ ጀብደኞችና ከህዝብ የራቁ ደናቁርት እንደሆኑ በቀላሉ የሚረዳ ይመስለናል። ለምሳሌ ቅጥረኛዉ ቄሴ በቦምብ ጨርሼያቸዉ ታሪክ ከሰራሁ በኋላ በእርግጠኝነት እወጣለሁ ወይም መቶ ፐርሰንት አመልጣለሁ፤ አለዚይም እራሴን አጠፋለሁ እንጂ እነሱስ አያገኙኝም ብሎ ለአለቆቹ ሲናገር . . . . "ሽማግሌዉን በራሱ መሳሪያ ግደለዉ እንጂ ከኛጋ መሳሪያ መላክ አይቻልም" ይሉ የነበሩት አለቆቹ "አይዞህ" መሳሪያ ማስገባት ቀላል ነዉ ፤ ሆኖም እኛ ስራዉ እንዲሰራ ብንፈልግም ያንተ ህይወት እንዲጠፋ አንፈልግም እያሉ ይህንን እንደ በሬ ሳሩን ብቻ እንጂ ገደሉን ያላየ ተላላ ፍጡር ወደ ገደሉ ይገፉታል። ቄሴ አልገባዉም እንጂ የሱና የወያኔ ፍቅር አንዳርጋቸዉን አስከገደለላቸዉ ድረስ ብቻ ነበር፤ ወያኔዎች ቄሴ በለስ ቀንቶት ዕቅዱ ቢሳካም ሸሽቶ ማምለጥ እንደማይችል በሚገባ ያዉቃሉ፤ ይህንን እያወቁ ነዉ አንተ ከሞትክ እኛ ትርፍ አይኖረንም እያሉ ለሱ የተጨነቁ እየመሰሉ እሳት ዉስጥ እንዲገባላቸዉ የሚገፋፉት።

የወያኔ ዘረኞች እንሰጥሃለን የሚሉት ገንዘብ፤ ክብርና ዝና አይኑን የሸፈነዉ ተላላዉ ቄሴ በሞት መንገድ ላይ እየተጓዘ . . . . "ምንም ችግር የለም" እናንተ መሳሪያዉን አምጥታችሁ ስጡኝና የአንዳርጋቸዉን ነገር ለኔ ተዉልኝ እያለ ሲወተዉት ተደምጧል። አንድ ቦታ ላይ የወያኔዉ የደህንነት ሹም የሙሉቀን መስፍን ወይም ቄሴ ስራ ለታሪክ እንደሚቀመጥና ለብዙ ኢትዮጵያዉያን ትምህርት እንደሚሆን ተናግሮ ነበር። እግዜር ይስጠዉ። ከዚህ አባባሉ መሬት ላይ ጠብ የሚል ነገር ያለም አይመስለንም። በእርግጥም ከሙሉቀን መስፍን ክህደትና ከዘመቻ ወያኔ ኦ ሚሊኒየም የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ትምህርት ቀስሟል ብለን እናምናለን። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የአፍሪካ ጋዜጠኞች የወያኔን ልማታዊ ጋዜጠኝነት አስተሳሰብ ተቹ

አዲስ አበባ ዉስጥ በተካሄደዉ ያለዉ 6ኛው የአፍሪካ ሚዲያ አመራሮች ፎረም የወያኔ ዋልጌ ምሁራን የፈጠራ ዉጤት የሆነዉንና ወያኔ ሌሎቹም የአፍሪካ አገሮች እንዲከተሉለት በማቀንቀን ላያ ያለዉን "የልማታዊ ጋዜጠኝነት" ጽንሰ-ሀሳብ አላስፈላጊና ትርጉም የለሽ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነዉ ሲሉ የአፍሪካ ጋዜጠኞች መተቻታቸዉ ተሰማ። ፎረሙ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች ችግሮቻቸውን ፊትለፊት አውጥተው መናገር ባለመቻላቸውም ወቀሳ አነሱንና በጉዳዩ እጁ አለበት ብለዉ ያመኑበትን የወያኔን አገዛዝ አዉግዘዋል። ጠ/ሚኒስትር ተብዬዉ ኃ/ማርያም ደሳለኝ በጉባዔዉ መክፈቻ ላይ ባደረገዉ ንግግር የፕሬስ ነጻነት በኢትዮጵያ መረጋገጡን በማውሳት ፕሬሱ ግን በውስጡ የአቅም ውስንነቶች እንዳሉበትና ይህን ችግር ለመፍታት መንግሰት እየሰራ መሆኑን ያለ ምንም እፍረት አፉን ሞልቶ ተናግሯል። ኃ/ማርያም ደሳለኝ ከነጻ ፕሬስ ጋር ፍጹም የማይተዋወቀዉንና በአለም ላይ ጋዜጠኖችን በማሰር አንደኛ የሆነዉን አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን አረጋግጧል ብሎ መናገሩ የራሱን ደጋፊዎች ጭምር ግራ አጋብቷል።

ኃ/ማርያም በዚሁ የመክፈቻ ንግግሩ በደፈናዉ ኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት አከባሪ መሆንዋን ከመናገር ውጪ በአገዛዙ ውስጥ ያሉ የፕሬስ ማነቆዎችን ለመደበቅ ሙከራ ቢያደርግም በጉባዔው ላይ ከደቡብ አፍሪካ ተጋብዘው የመጡ አንድ ተሳታፊ በኢትዮጵያ ከ70 በላይ ፕሬሶች ባለፉት ዓመታት በመንግስት ጫና መዘጋታቸውን፣ ሰባት ያህል ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ተከስሰው በእስር ላይ እንደሚገኙ መረጃ እንዳላቸው በመጥቀስ የኢትዮጵያን መንግስት ተችተዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ ተሳታፊ የጉባዔው መሪ ቃል አፍሪካ ትናገር እንደሚል በማስታወስ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችን ስለችግራቸው ለምንድነው የማይናገሩት በሚል ጠይቀዋል። ይህ ያለመናገራቸው ሁኔታ በእርግጥም ችግር መኖሩን እንደሚጠቁም ጠቅሰዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሃሳባቸውን በመግለጻቸው ብቻ በሽብርተኛነት ተከስሰው በእስር ላይ የሚገኙ ጋዜጠኞች መኖራቸውን በመጥቀስ ጉባዔው በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽ እንዲወያይና አቋዋሙን ሊገልጽ እንደሚገባ ተናግረዋል።

አዲሱ የወያኔ የኮምኒኬሽን ሚኒስትር ሬድዋን ሁሴን ኢትዮጵያ የፕሬስ መብት ረጋጭ አገር ሆና እንዲህ ዓይነት አህጉራዊ ጉባዔ ልታዘጋጅ አይገባትም በሚል ከአንዳንድ ወገኖች የቀረበውን ትችት በተመለከተ ተጠይቆ እነዚህ ወገኖች የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ የማያውቁ ጸረ ልማት ሃይሎች ናቸው በማለት የተለመደዉን ወያኔያዊ የማጣጣል ምላሽ ሰጥቷል። ከዚህ ተጨማሪ የአፍሪካ ሚዲያ መሪዎች ፎረም ኢትዮጵያ ዉስጥ ከፍተኛ የፕሬስ አፈና መኖሩን በይፋ ከመናገሩም በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለቸዉ ጋዜጠኞች መታሰራቸውንና በርካታዎች መሰደዳቸውን በመጥቀስ ኢትዮጵያ በአለማችን ጋዜጠኞች ከሚሰደዱባት አገራት በሶስተኛ ደረጃ የምትገኝ አገር ናት ብሏል።

## ትግሉ መሯል፤ እኛም ዝግጁዎች ነን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በአንፃሩ ደግሞ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል የተደራጀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሆንም ምን ያህል ወያኔን እንቅልፍ እንደነሳ ተጨባጭ ማስረጃ ሆኗል። ይህ ለነፃነት ታጋዮች ከፍተኛ የስነልቦና ብርታት የሚሰጥ ነገር ሆኖ ተገኝቷል።

በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል የተቃጣበትን ጥቃት ከማክሸፍ በተጨማሪ የወያኔን ገበና ማጋለጥ በመቻሉ የመጀመሪያው ሁነኛ ድል ተቀዳጅቷል።

ግንቦት 7፣ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "ወያኔ ኦ ሚሊኒየም" ኦፕሬሽንን ላከሸፉ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል አመራርና አባላት ያለውን አድናቆት ይገልፃል። ለወደፊቱም ተመሳሳይ ጥቃቶች ሊደርሱ የሚችሉ መሆኑን በመገንዘብ የመከላከል ብሎም የማጥቃት ኃይሉን እንዲያጠናክር ይመክራል።

የንቅናቀዓችን እና የሕዝባዊ ኃይሉ አመራርና አባላት ለመስዋዕትነት የተዘጋጁ ናቸው። "ወያኔ ኦ ሚሊኒየም" ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ትግላችን ይገታ ነበር ማለት አይደለም። ትግላችን መስዋዕትነትን የሚጠይቅ መሆኑን እናውቃለን። ጓዶች ሲወድቁ ሌሎች ሺዎች አርማቸውን አንስተው ትግሉን ይቀጥላሉ።

ትግሉ የሚጠይቀንን መስዋትነት ከፍለን ወያኔን ከሥልጣን አስወግደን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሆነባት ኢትዮጵያ እንደምትኖረን እርግጠኞች ነኝ።

ትግሉ መሯል፤ እኛም ዝግጁዎች ነን።

ድል ለግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

## በአዲስ አበባ ፍተሻው በአዲስ መልክ ተጀመረ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፈዉ ሳምንት አልሸባብና በኤርትራ መንግስት የሚታገዙ ሽብር ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ስፍራዎች የሽብር ጥቃት ለመፈፀም እየተዘጋጁ መሆናቸውን የሚያሳይ አስተማማኝ መረጃ አለኝ ካለ በኋላ አዲስ አበባና ነዋሪዎቿ ከወትሮው ለየት ባለ የፍተሻ ማዕበል መዋጣቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገለጹ። የፌዴራል ፖሊስ የጸረ ሽብር ግብረ ኃይል በየክልሉ በሚገኙ ሆቴሎች፣ ሕዝባዊ ተቋማትና የፍተሻ ኬላዎች ላይ የሚሰሩ የፍተሻ ስራተኞች ተግባራቸውን ከወትሮ በተለየ ጥንቃቄ ና አትኩሮት ማከናወን እንዳለባቸውም በአጽንኦት ያስጠነቀቀ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ በተለይ በሆቴሎችና በሕዝባዊ መዝናኛዎች ለየት ያሉ ፍተሻዎች እየተካሄዱ ነው።

በካዛንቺስ አካባቢ የሚገኙ ራዲሰን ብሉና ጁፒተር ኢንተርናሽናል ሆቴሎች የመፈተሻ ዘመናዊ ማሽኖች ጭምር ገዝተው ለመግጠም የተገደዱ ሲሆን አነስተኛ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሰዎች መፈተሸ ኤሌክትሮኒክስ የደህንነት መፈተሻ መሳሪያዎችን በብዛት በመሸመት በስራ ላይ እያዋሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ፖሊስ ጠርጥሬአቸዋለሁ ባላቸው እንደ ሳሪስ ባሉ አካባቢዎች ድንገተኛ የቤት ለቤት ፍተሻ ሰሞኑን ያካሄደ ሲሆን በአዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶች ላይም ተሽከርካሪዎችን በማስቆም ረጅምና አሰልቺ ፍተሻዎችን ሲያካሂድ ታይቷል።

በተጨማሪም ሆቴሎቻቸውንና መኖሪያ ቤታቸውን የሚያከራዩ ባለንብረቶችና ባለ ይዞታዎች በተለይ የውጭ ሀገር ዜጎችንና የማያውቋቸውን ኢትዮጵውያንን አድራሻ በአግባቡ መዝግበው በመያዝ መረጃን ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ የህግ ግዴታ እንዳለባቸው መግለጫው በጥብቅ አስጠንቅቋል። በተመሳሳይ መኪናዎቻቸውን የሚያከራዩ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለታክሲዎች የደበኞቻቸውን ማንነት የሚገልጽ ሙሉ መረጃ የመያዝና የማሳወቅ እንዲሁም የሚጭኗቸውን ማናቸውንም ዕቃዎች የማወቅ ግዴታም ያለባቸው መሆኑን የፀረ ሽብር ግብረ ሀይሉ አስታውቋል። ህብረተሰቡ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥመው ሁኔታውን በአቅራቢያው ላሉ የፖሊስና የፀጥታ ሀይሎች እንዲያሳውቅም አሳስቧል።

የጋራ የፀረ ሽብር ግብረ ሃይሉ በዚህ ሳምንት በሰጠዉ መግለጫ ባለፈው ጥቅምት 3 ቀን 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ አካባቢ ለሽብር ተግባር ሲሰናዱ በራሳቸው ላይ ባደረሱት አደጋ ህይወታቸው ጠፋ በተባሉ ሁለት ሶማሊያዊያን አሸባሪዎች ጉዳይ ላይ ምርመራ እየተደረገ መሆኑን ተናግሯል። ሆኖም እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በወቅቱ የኢትዮጵያና የናይጀሪያ ብሄራዊ ቡድኖች የሚያደርጉትን የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ውድድር በሚከታተሉ የስፖርት አፍቃሪዎች ላይ አደጋ ለማድረስ ዓላማ እንደነበራቸው የሚያሳዩ መረጃዎች መገኘታቸውን መግለጫው በተጨማሪ ያስታውቅ እንጂ ፍንዳታው በእርግጥም በአሸባሪ ቡድኖች ስለመፈጸሙ ለሕዝብ እስካሁን በተጨባጭ የገለጸው ነገር የለም። በዚህ ምክንያት ብዙ ወገኖች በ1997 ዓ.ም ገዥው ፓርቲ ራሱ ፈንጂ ቀባሪ፣ ራሱ አምካኝ የሆነበትንና የተጋለጠበትን ክስተት በማስታወስ ነገሩን በጥርጣሬ እየተመለከቱት ይገኛሉ።

## በሬ ሆይ ሳር ሳሩን አየህ ገደሉን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በገንዘብና በማይረባ ስልጣን ተደልለዉ የአገራቸዉን ብሔራዊ ጥቅም ለጠላት አሳልፈዉ የሰጡና በራሳቸዉ ነፃነት ላይ የዶለቱ ከሀዲ ኢትዮጵ ዉያን ታሪክ ሲነሳ ከሀዲዉ ሙሉቀን መስፍን የመጀመሪያዉ ሰዉ አይደለም፤ የመጨረሻዉም አይሆንም። የሙሉቀንን ክህደት ልዩና ትንግርታዊ የሚያደርገዉ አማራን አጠፋለሁ ብሎ ትግል የጀመረዉና "እናንተ ሽንታም አማሮች" ምን እንዳትሆኑ ነዉ . . . እየረገጥን እንገዛችኋለን እያለ የሚደነፋዉን የጠላቱን የወያኔን ትዕዛዝ ተቀብሎ ለራሱና ለወገኖቹ መብትና ነጻነት መከበር የሚታገለዉን ሰዉ ለመግደል ድንበር አቋርጦ ጎረቤት አገር መሄዱ ነዉ።

ቄሴ ወይም ሙሉቀን መስፍን "አንተ የምትሰራዉ ስራ በመስሪያ ቤታችን ታሪክ የመጀመሪያዉ ትልቅ ታሪክ ነዉ" ተብሎ ሲነገረዉ እዉነት መስሎት አይዟችሁ ታሪክ ሰሪቹ እመጣለሁ ብሎ ሲናገር በተከታታይ ይደመጣል። በእርግጥም ቄሴ ተልዕኮዉ ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ አገር ዉስጥ ሰላማዊ ዜጎችን ከመግደል ዉጭ ሌላ ይህ ነዉ ተብሎ የሚጠቀስ ስራ ሰርቶ የማያዉቀዉ የወያኔ ደህንነት መስሪያ ቤት የግንቦት ሰባት መሪዎችን በመግደሉ ሌላ ቢቀር ወያኔና ደጋፊዎቹ ዛሬስ አለፈልህ ብለዉ ያጨበጭቡለት ነበር፤ ነገር ግን ዕድሜ ለጀግኖቹ ግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይሎች የኃ/ማሪያምንና የጌታቸዉ አሰፋን ሴራ "እርሟን ብታፈላ አተላ" አደረጉት። ኃ/ማሪያም ደሳለኝና ጌታቸዉ አሰፋ ማወቅ የሚገባቸዉ ነገር ቢኖር ታሪክ የሚዘክራቸዉ ትልልቅ ስራዎች የሚሰሩት በትልልቅና አርቆ አስተዋይ በሆኑ ሰዎች ነዉ እንጂ እንደነሱ ዛሬ በልቼ ነገ ልሙት በሚሉ ትንንሽና ምናምንቴ ሰዎች አይደለም። የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይሎች የወያኔንና የዘረኛ ስርዐቱን ዝቅጠትና ዉድቀት በሚተርከዉ የታሪክ ድርሳን ዉስጥ የመጀመሪያዉን ምዕራፍ "ወያኔ ዋ ሚሊኒየም" ብለዉ ጀምረዉታል፤ የመጨረሻዉ ምዕራፍ "ወያኔና ዘረኛ ስርዐቱ" ተደመሰሱ ተብሎ በቅርብ ግዜ እንደሚጻፍ ምንም ጥርጥር የለንም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

# የሃያ ዓመት ደብዳቤ

ከፈቃደ ሸዋቀና (ክፍል 2 )

በኔ ስደት ሀገር ደግሞ ጋዜጠኛ ከህግ የወጡና ህላፊነታቸውን ያጓደሉ የመንግሥት ባለስልጣናትን እያገላበጠ ይጠብሳል። በየቀኑ መንገድሽ ላይ እየቆመ አላሳልፍ የሚል መንግሥት የለም። አርፎ ስራውን የሚሰራ ሰው ባመት አንድ ወይም ሁለት ቀን ወይ የታክስ ዕለት ወይም መንጃ ፈቃዱን ለማሳደስ ሲሄድ ነው ከመንግሥት ጋር ፊት ለፊት የሚገናኘው። ባጭሩ እዚህ ህዝብ የሚነዳው መንግሥት እንጂ ህዝብ እንደ እንስሳ መንጋ የሚነዳ መንግሥት የለም። እኔ ልጅሽ በሀያ አመት ውስጥ ከፖሊስ ጋር የተገናኘሁት አንድ ቀን ብቻ ነው፥ ያውም በገዛ ጥጋቤ። 65 ማይል በሰዓት የተፈቀደ አውራ መንገድ ላይ በ85 ስነዳ አነዳዴን አይቶ ይከታተለኝ የነበር ፖሊስ ከኋላዬ መጥቶ አስቆመኝ። ብዙ አላስቸገረኝም፡ የመቀጫ ትኬቴን ስጥቶ አደጋ ላይ እንዳልወድቅ መክሮ ሰላምታ ሰጥቶ ባምስት ደቂቃ ውስጥ አሰናበተኝ። ቢቃ ይኸው ነው።

የዚህ አገር መንግስት ቴሌቪዥንም ሬዲዮም ስለሌለው ማታ ቤቱ ስገባ እደነቁራለሁ ብሎ ስጋት የለም። ስልጣንና እውቀትን አደባልቆ የሚያይ ባለስልጣን ሺ ጊዜ አብልጬ በማውቀው ጉዳይ ላይ ሊያስመልሰኝ እስቲተናነቀኝ ዉሸት ሊግተኝ ይንጠራራብኛል ብሎ ስጋት የለም። ታጋይ፣ ካድሬ፣ ቀበሌ ብሎ ነገርማ ባገሩ የለም። የመንግሥት የድጋፍ ሰልፍ፥ የተሀድሶ፥ የግምገማና የንቃት ስብሰባ የሚባል የስራ ፊት ስራ የለም። ድሀ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም በሚል ፍልስፍና ነጋ ጠባ መዋጮ የሚጠይቅ መንግሥት የለም። እዚህ እንደ ጉራፈርዳና ቤኒሻንጉል ከክልሌ ውጡ ብሎ የሚያስቸግር መንግሥት የለም። ከየትም ሄዶ የትም ርስት ገዝቶ መኖር ይቻላል። በገዛሁት ርስት ላይ ደግሞ ነዳጅ ባወጣበት ወይም ማዕድን ባገኝ አምጣ ወይም ጥለህ ሂድ የሚለኝ የለም። ያለሁበት ሀገር ሀብታም የሆነው በምትሐት እንዳይመስልሽ። እዚህ አገር ክልል ማለት ሀብታም ገበሬዎች ከብት የሚያረቡበት ሰፋፊ በረት ነው። አንቺ ጋ የመንግሥት ሹም ኤክስፐርትና ምሁራንን ሰብስቤ ካላሰለጠንኩ ይላል። የዚህ አገር ሹማምንት ምንም የተማሩ ቢሆኑም እንኳን ከባለሞያ ከፍለው ምክር ይገዛሉ። እዚህ አገር ያሉ ፖለቲካኞች አብዛኛውን ጊዚያቸውን የሚያጠፉት ስለነገ በመጨነቅ እንጂ ባለፈና ባጨቃጫቂ ታሪክ ላይ በመነታረክ አይደለም። ታሪክ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንጂ በየሜዳውና በየቀበሌ ስብሰባ ላይ የማንም ጥራዝ ነጠቅና ረኸጥ ወሬኛ እንዳሻው ሲያቦካው የሚውል ሊጥ አይደለም። እና ታዲያ ይህን የመሰለ አገር ለምን አልወደውም?

ደሞ እኩያዬ ካልሆነ አገር ጋር ለምን ታወዳድረኛለህ ትይኝ ይሆናል ያንቺ ነገር። አንቺ እኮ በድሜ ከሁለት ሺ አምስት መቶ ዓመት በላይ ስለምትበልጭው አገር ነው የማወራው። ባለራዕዮቹ መሪዎቻቸው ምንም ባሪያ ፈንጋይ ቢሆኑና ቢደላቸውም ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ራሳቸውን ከበታቹ ሆነው ሊታዘዙት ወስነው ባወጡት ሕገ መንግሥት ነው ዛሬ ድረስ የሚተዳደሩት። እስቲ አስቢው እነሱ ከሁለት መቶ አመት በፊት ያወጡትን ዘዴ ማውጣት አንቺ ዛሬና አሁን እንዴት ያቅትሻል? ደሞ አብሬ ኖሬ ሳያቸው ከቆዳ ቀለም በቀር ካንቺ ልጆች የተለየ የተፈጥሮ ባህርይ ምንም የላቸውም። እንደኛው ሰዎች ናቸው። አንዳንዶቹን ዛሬ የምናስተምራቸው እኮ እኛው ያንቺው ልጆች ነን።

ይህንን አንዳንዴ በዕዝነ ልቦናዬ እየመጣሽ አንተ ከሃዲ በሌላ ለወጥከኝ አይደል፣በችግር አሳድጌ አስተምሬህ ዛሬ ሲመችህ ከዳኸኝ አይደል? እያልሽ የምትጨቀጭቂኝን ስለመድህኒዓለም ብለሽ ተይኝ። እንዴ! ምን አርግ ነው የምትዪኝ? ፈረንጅ አገር እኮ ስማር ከርሜ ወዳንቺ ከተመለስኩ ዓመት እንኳን አልሞላኝም ነበር ሹሞችሽ ያቅሜን ያውም በድህነት ላገለግልሽ ከምሰራልሽ ሥራ ሲያባርሩኝ ዝም ብለሽ ያየሽኝ። መካር ተው አትሂድ ሲለኝ ነው እኮ ዘልዬ ወዳንች የመጣሁት። አዲሶቹ ገዢዎችሽ ሲመጡ ከምር በጎ ነገር ያመጡ ይሆናል ብዬ ልረዳቸው ተነስቼ ነበር። ጥላቻ አሸነፋቸው መሰለኝ ጠሉኝ። ያገኘሁትን ሰርቼ እንኳን እንዳልኖር የሚያደርጉኝን ነገር አይተኛል። ጎዳና ተዳዳሪነት ተመኙልኝ። ጥላቻቸው እንዳይጋባብኝ ከፉኛ ፈርቼ ነበር። ጥላቻ ጠይውን ይበልጥ እንደሚጎዳ ስለማውቅ መጥላት አልወድም። በድርጊታቸው እንድጠላቸው ሳይሆን እንድንቃቸው ስላደረጉኝ አመሰግናቸዋለሁ። በዚህ ላይ ያንን አስራ ስባት ዓመት የልጅነት እድሜዬን እንዴት እንዳሳለፍኩት ታውቂያለሽ። ነፍሴ የተረፈችው የሎተሪ ያህል ዕድል አግኝታ እንጂ ጓደኞቼማ የት ወድቀው እንደቀሩ የምታውቂው አንቺው ነሽ። እናት አባቴ ለኔ ብለው ከጠላት ተዋድቀው ባቆዩት ሀገር እንዴት ነው ዘላለም አጎንብሼና ፈርቼ እንድኖር የምትፈርጅብኝ? ለውለታቸው ክፍያ አልጠየቁ። ሌላ ቢቀር ለፍተው ያስተማሩት ልጃቸው ቀና ብሎ መሄድ ሲከለከል ምን ይሰማቸዋል? ይህን የቁም ሞት እየኖርኩ ካንቺ ጋር ብኩራመት ምን እጠቀምሻለሁ? ተይ እንጂ። እንዴት ነው ባንቺ ብሶ የምትውቅሽኝ። ለመሆኑ መንዝ ጌራና ላሎ መጋጠሚያ ቆላ ውስጥ ያለውን አመጠኜ ዋሻን አንቺም እንደሰው ረሳሽው? አመጠኜን ትልቁን ያርበኞች ምሽግ ዋሻ ነው የምልሽ ረስተሸው እንደሆን። ከዚያ እየወጡ ነበር ጣሊያንና የባንዳ ሰራዊቱን እብድና እውር ያደርጉት የነበረው የኔ ዘመዶች። ጣሊያን ምሽጉን መስበር ሲያቅተው ያገኘው ሰይጣናዊ ዘዴ የመርዝ ጋዝ የያዘ በርሜል ካፋፍ ዋሻው በር ላይ አንጠልጥሎ ማፈንዳት ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ አንበሶች እዚያው በመርዝ ጭስ ፈጁቸው። አንድ ዘመዴ ነበር በልጅነቴ አጽማቸውን እያሳየ እያለቀሰ ያስነብበኝ። እንደ ውለታና ታሪክ አክባሪ አገሮች ብትሆኚ ኖሮ የኔን የዘመዳቸውን ቀና ብሎ መሄድ ማስከበር በቻ ሳይሆን ለጀግኖቹ አመጠኜዎች በቦታው ሀውልት አሰርተሽ የቱሪስት ማዕከል ታደርጊው ነበር። አንቺ ደስ የሚልሽ የገዛ ወንድሙን የገደለ የርስበርስ ጦረኛ ጀግና እያሉ ማሞገስና ሀውልት መስራት ሆነ። ቁርጡን ልንገርሽ። ዉለታ በላ ሀገር ባለውለታ ትውልድ አያፈራም። ችግርሽም ይህ ይመስለኛል። ያገለገሉሽን ማስከበር አቅቶሻል። ካንቺ አልለይም ብሎ ሙጥኝ ብሎ የሚኖረውን እኔን፣ አስተማሪዎቼንና ያስተማሪዎቼን አስተማሪዎች ያስተማረ የሶስት ትውልድ መምህር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን ምን እንደምታስደርጊው የማላውቅ መሰለሽ? የሚወርድብትን የመደዴ ስድብ ሀይ ማለት ያቅትሽ፤ እንዴት ወህኒ ቤት በሰማኒያ አመቱ ታሳጉሪዋለሽ? ኑ ሞግቱኝ ስላለና ስለተከራከረ? ሃሳቡ ተቀባይነት የለውም ቢባል እንኳን ይህ ሁሉ ይገባዋል? ትንንሾቹ ልጆችሽ ትልልቆቹ ባለከብረ ህሊናዎች ሲዋረዱ እያየን እንዴት ላንቺም ለራሳችንም ክብር እንዲኖረን ትጠብቂያለሽ።

ደሞ ለምን እዚሁ ሆነህ እንደ አገሩ ልማድ ጠምንጃ አንስተህ ሸፍተህ አልሞከርከውም እንዳትዪኝ። ይህን ርስ በርስ እየተጋደሉ ጀግና እየተባባሉ የመኮፈስ ወግሽን አልወደውም። በዚህ ላይ ጠመንጃና መጥረቢያ አልወድም ብዬሻለሁ። ከፈለግሽ ፈሪ ልትዪኝ ትችያለሽ። መብትሽ ነው። ጠመንጃ የጠላሁት ገና ትንሽ ልጅ ሆኜ ነው። ጥምቀት ለማክበር ይመስለኛል በዚያውም ዘመድ ለመጠየቅ ባላገር ዘመዶቼ ጋ ሄጄ ነበር። አንድ እንደብርቅ የሚወደኝ አጎቴ ተኩስ ላስተምርህ ብሎ አረህ ይዞኝ ወረደ። ጭር ካለው ቆላ ውስጥ ከፊቴ ኢላማ እያሳየ ሲያስተኩሰኝ ያሳየኝን ኢላማ ሁሉ አልመታሁትም። መጨረሻ ላይ በይ አሁን ግዳይ ትጥያለሽ አለና ከበላያችን አለው ተረተር ላይ መሬት የሚጭሩ ዝንጀሮዎች መሀል አስተኮሰኝ። (ሞት ሲመጣ ተሳሳትኩ ብሎ እንዲመለስ ነው አሉ የኔ ዘመዶች ወንዱን አንቺ ሴቱን አንተ እያሉ የሚጠሩት)። ዝንጀሮዎቹ ደንብረው ከሸሹ በኋላ ቦታው ደርሰን ስናይ አንዲት ግልገል ዝንጀሮ አይኗን እያንከራተተች ስታጣጥር አገኘናት። አጎቴ ደስ የሚለኝ መስሎት "የኔ አምበሳ ደረቷን ነው ያገኘሸው" እያለ ሊያኩራራኝ ሲሞክር እኔ በሀዘን ተጨማድጄ መፈጠሬን ነበር የጠላሁት። ለጨዋታ እየዘለለሁ የወጣሁት ልጅ በሀዘን አጎንብሼ ነው የተመለስኩት። ያን ሰሞን ህልሜ ሁሉ ቅዠት ሆኖብኝ ከረመ። ከዚያን ቀን በኋላ ጠመንጃ ያስጠላኛል። እኔ ዝንጀሮ ስለገደልኩ ያን ያህል ሌት ተቀን ያባነነኝን ቅዠት አስታውስና ሰውን ያህል ፍጡር አነጣጥረው ገለው በሰላም እንቅልፍ ይዟቸው የሚያድር ሰዎች እንዴት ከራሳቸው ጋር እንደሚኖሩ መገመት ይከብደኛል። እናም እናቴ እንደፍጥርጥርሽ ሁኚ እንጂ እኔ ሰው ላይ አልተኩስም። በዚህ የሚገኘው ጀግንነትም ባፍንጫዬ ይውጣ።

እምዬ ብዙ ከፉ አናገርሽኝ። ጠልቼሽ ግን እንዳይመስልሽ ይህን ሁሉ የምወርድብሽ። እጆችሽን ዘርግተሽ ለተሻለ ዘመን እንደምትጸልዪም አውቃለሁ። እጅሽ ዝሎ ከመሰብሰቡ በፊት ግን አምላክሽን ወይ ውረድ ወይ ፍረድ ብለሽ ወተረሽ ብትይዢው ይሻላል። የመከራሽን ጊዜ ያሳጥርልሽ ይሆናል። አትፍረጂብኝ እናት አለም። እሁን ብመጣም የማረግልሽ ነገር የለም። ሰርቶ ያልጠገበ፣ ምን ልፍጠር ያለ ጎረምሳ ሽንተሽ እሁን በስተርጅና ብመጣ ምንም አላደርግልሽም። ልጅ ሆኜ ሳረጅ የበግ ርባታ ገበሬ እሆናለሁ የሚል ምኞት ነበረኝ። ያን ጊዜ "ርስት በሺ ዓመቱ ለባለቤቱ" ይባል ስለነበር ትውልዴን ቆጥሬ በግ ማገኝ የሚሆን መሬት የማጣ አይመስለኝም ነበር። ዛሬ ባለርስቱ መንግስት ስለሆነ ድፍን ኢትዮጵያ የመንግሥት ጭሰኛ ሆኗል። ኩርማን መሬት በየከተማው በቶኪዮ ዋጋ በመጋዘ እንደሚሸጥም ሰምቻለሁ። አባቶቻችን "የልጅ ደንጋዝ ያባቱን መሬት ይጋዛ" ይሉ ነበር ርስቱን በጉልበተኛ ተነጥቆ መልሶ የራሱን ርስት ተጋዝቶ የሚያርስ ገበሬ ሲያዩ። ዛሬ አብዛኛው ልጅሽ ደንገዝ ያባቱን መሬት መጋዛትም እንዳቃተው እሰማለሁ።

**( ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)**

# ኢትዮጵያውያን በሳውዲ አረብያ በወገኖቻችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የኢትዮጵያ ህዝብ በገዛ አገሩ ሰርቶ መኖር እንዳይችል የሚያደርግ ጠማማ የኤኮኖሚ ፖሊሲ ቀይሶ አገራችንን የባዕዳን መፈንጪያ ያደረጋት ወያኔ የራሱን ዜጎች አፈናቅሎ መሬት ለባዕዳን መስጠቱ ሳያንሰዉ እነዚሁ ባዕዳን አገራቸዉ ዉስጥ ኢትዮጵያዉያንን እገደሉ ጎዳና ለጎዳና ሲጎትቱ አይቶ ዝም ማለቱ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን አስቆጥቷል። በተለይ ዛሬ ኢትዮጵያዉያን እህቶቻችንንና ወንድሞቻችንን ባገኙበት ቦታ ሁሉ የሚደበድቡትና የሚገድሉት የሳዉዲ ዜጎች ኢትዮጵያ ዉስጥ መጠነ ሰፊ መሬት በርካሽ ተሰጥቷቸዉ እያረሱ ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብሱ ቱጃሮች ሆነዋል። በአንጻሩ እነሱ ከአገሩ ያፈናቀሉት ኢትዮጵያዊ ሳዉዲ ዉስጥ እንደ እንስሳ እጁን ታስሮ መንገድ ለመንገድ መጎተቱ የሳዉዲዎቻችን ጭካኔ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ኢሰብዓዉያን መሆናቸዉንም ያሳያል።